# በአገር ውስጥ ያልተመዘገቡ ዝርያዎች ከውጭ አስገብቶ የማባዛትና መልሶ የመላክ ማስፈጸሚያ መመሪያ

**456/2013**

መመሪያ ቁጥር 003/2012

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

## መግቢያ

በአገር ውስጥ ያልተመዘገበ ዝርያን በአገር ውስጥ ተመርቶ ለውጭ አገር ገበያ የሚቀርብበትን በተመለከተ ግን እንደ አስፈላጊነቱ በሚኒስትሩ በሚወጣ መመርያ እንዲወሰን የተደነገገ በመሆኑ፤

ዘር አምራቾች በአለም አቀፍ የዘር ንግድ ገበያ ውስጥ ለመግባትና ውጤታማ ለመሆን ገበያው የሚፈልጋቸው ምርቶች በብዛትና በጥራት ይዘው መቅረብ ግድ ስለሚላቸውና በአገር ውስጥ የተመዘገቡና የተለቀቁ ዝርያዎች ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ ላለው ፍላጎት የሚመጥኑ ባለመሆናቸውና ተወዳዳሪነታቸውም ዝቅተኛ በመሆኑ፤

የባለሃብቶች በዘር ማምረት መሳተፍ የሥራ ዕድል የሚፈጥርና የውጭ ምንዛሬ ግኝት የሚያሳድግ በመሆኑ፤

በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀጽ 17 እና በዕፅዋት ዘር ደንብ ቁጥር 375/2008 አንቀጽ 18(2) (ለ) አንቀጽ 34 (1) በተደነገጉት መሠረት ሚኒስቴሩ ይህን መመርያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

፩/ አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"በአገር ውስጥ ያልተመዘገቡ ዝርያዎች ከውጭ አስገብቶ የማባዛትና መልሶ የመላክ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር**456/2013 " ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

፪/ ትርጓሜ

በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 እና በዘር ደንብ ቁጥር375/2008 ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረግ በድጋሚ ትርጉም መስጠት ሳያስፈልግ የተሰጣቸውን ትርጉም የሚይዙ ሆኖ:-

ሀ/ "በአፈር ላይ ያልተመረተ" ማለት ለዘር ብዜት የሚገባው ዘር ከአፈር ጋር ቀጥተኛ ንክኪነት ሳይኖረውና ከዕፅዋት ተባይ ተሸካሚ ነጻ ሆኖ የተመረተ ማለት ነው፤

ለ/ "ዕፅዋት ተባይ ተሸካሚ" ማለት አንድ ተባይ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላው አካባቢ ለመጓጓዝ የሚያስችለው አካል ነው፡፡

ሐ/ "የዕጽዋት ጤንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት"፡ ማለት አግባብ ያለው አካል ለዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ የሚሰጠው የምስክር ወረቀት ማለት ነው፤

መ/"ወደ አገር ውስጥ ከመግባት የተከለከለ የዕጽዋት ዝርያ"፡ ማለት በዕፅዋት ኳራንታይን ሕግ መሰረት ወደ አገር ውስጥ ከመግባት የተከለከሉ የዕፅዋት ዘሮችን ይመለከታል፤

ሰ/ "አነስተኛ ይዞታ ያለው አርሶ አደር " ማለት በግብርና ሥራ የተሰማራ ሆኖ ኃላፊነቱ በተወሰነ በግል ማህበር ወይም በሽርክና ያልተመዘገበ ሰው ነው፤

ረ/ "ያልተመዘገበ ዝርያ" ማለት በአገሪቱ የዕፅዋት ዝርያ መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ ያልሰፈረ ዝርያ ማለት ነው፡፡

ሠ/ "ጥብቅ ግብርና" ማለት ተለይቶ በሚታወቅ አካባቢ በዘር ምክንያት ስለ ሚፈጠር አሉታዊ ተጽዕኖ በተቆጣጠሪው አካል ክትትልና ቁጥጥር የሚካሄድ ግብርና ነው፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

፫/ የተፈጻሚነት ወሰን

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው ከውጭ አገር የመጡ ያልተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያዎች መነሻ ዘሮች አገር ውስጥ በጥብቅ ግብርና እንዲባዙና ወደ ውጪ ለመላክ በተፈቀደላቸው የዕፅዋት ዝርያዎች ዝርዝር በተገለጹት ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል:: እነዚህ ዝርያዎች ሚኒስቴሩ በየጊዜው በሚያወጣው ዝርዝር መሰረት የሚገለጽ ይሆናል፡፡

፬/ የመመሪያው ዓላማ

በውጭ አገር ገበያ ላይ ተፈላጊነት ያላቸውና በአገር ውስጥ ያልተመዘገቡ ከውጭ የሚመጡ የዕፅዋት ዝርያዎች በአገር ውስጥ መመዝገብ ሳያስፈልጋቸው የሚባዙበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ለውጭ ገበያ ብቻ እንዲቀርቡ በማድረግ አገሪቱ ከውጭ ንግድ ያላትን ተጣቃሚነት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሳዳግ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ዝርያዎች ለማስገባትና ወደ ውጪ ለመላክ መሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች

፭/ ያልተመዘገበ ዝርያን ለማስገባት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፡

ሀ/ ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው ለጥብቅ ግብርና የሚሆን መስፈርት ማሟላቱ ተረጋግጦ ያልተመዘገበ ዝርያን አባዝቶ ወደ ውጪ ለመለክ ከሚኒስቴሩ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ያለው፤

ለ/ ከሚኒስቴሩ የማስገቢያ ፈቃድ/Import permit/ ያገኘ፤

ሐ/ ከመነጨበት አገር ዝርያው ስለመመዝገቡ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤ሆኖም ያልተመዘገበ ከሆነ የአገሪቱን የምዝገባ ሥርዓት ማለፍ ይኖርበታል፤

መ/ ከጭነቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የግዥና የርክክብ ሰነድ ማያያዝ የሚችል፡

ሰ/ የዕፅዋት ኳራንቲን፣ የደህንነት-ህይወትና ብዝሃ ህይወት የሚጠየቁትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የማባዛት ሂደት አፈጻጸም

፮/ የተፈቀደ ያልተመዘገበ ዝርያን ያስገባ ማንኛውም ሰው ያስገባውን ዝርያ የራሱ ወይም በሌላ አልሚ ማሳ ላይ ተቆጣጣሪው አካልን በማሳወቅ በውል ላይ ተመስርቶ በጥብቅ ግብርና ማባዛት ይችላል፡፡

፯/ በአንቀጽ 6 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ያልተመዘገበ ዝርያን ከውጭ አገር ያስገባ ማንኛውም ሰው በሌላ አልሚ ማሳ የሚያባዛ ከሆነ የብዜት ሂደቱን ሙሉ በሙሉ በጥብቅ

ግብርና መካሄዱን አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ አካል የተረጋገጠ የውል ስምምነት ሰነድ ማቅረብ የሚችል::

፰/ ያስገባውን ዝርያ በኮንትራት ስምምነት ጥብቅ ግብርና ባልሆነ ሁኔታ በአርሶ አደሮች ማሳ ላይ ማባዛት አይችልም፡፡

፱/ ያልተመዘገበ ዝርያ ዘር የተባዛበት ማሳ ለሌላ ተግባር ከመዋሉ በፊት አፈሩ ከዘር ጋር በተያያዘ የመጣ የዕጽዋት በሽታና ተባይ ነጻ ስለመሆኑ በተቆጣጣሪው አካል መረጋገጥ አለበት፡፡

፲/ ዝርያው ስምምነት ከተደረሰበት ማሳ ውጭ ሲባዛ ቢገኝ አግባብ ባለው በሀገሪቱ ህግ መሰረት ተጠያቂ ለመሆን ሃላፊነት የሚወስድ መሆን መቻል አለበት፡፡

፲፩/ ያስገባውን ዝርያም ሆነ ከዝርያው የሚገኘን ምርት ሌላ ወገን እንዲጠቀምበት ወይም ገበያ ላይ እንዲያውለው. በሽያጭም ሆነ በስጦታ አሳልፎ መስጠት አይችልም፡፡

፲፪/ያልተመዘገበን ዝርያ ተረፈ ምርት ዘር ያለው ከሆነ ለሰው ለምግብነትም ሆነ ለእንስሳት መኖ ግልጋሎት በማንኛውም መልኩ በአገር ውስጥ በሽያጭም ሆነ በስጦታ ጥቅም ላይ መዋል አይችልም፡፡

፲፫/ በአንቀጽ 12 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ተረፈ ምርቱ ዘር ያለው ከሆነ የተገኘውን ምርት በጥብቅ ግብርና ማሳው ተቀጣጣሪውን አካል በማሳወቅ መልሶ ለማልማት ሊውል ይችላል፡፡ ሆኖም ጥቅም ላይ የማይውል ከሆነ ተቆጣጣሪ አካል በሚሰጠው ምክረ-ሃሳብ መሰረት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

፲፬/ ያስገባውን ዝርያ በሚያባዛበት ሂደት ውስጥ በተገባው ውልና ስምምነት መሰረት እያባዛ መሆኑን አግባብ ላለው የመንግስት የቁጥጥር አካል ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት
## የተባዛን ያልተመዘገበ ዝርያ ወደ ውጭ የመላክ ሂደት አፈጻጸም

፲፭/ ያልተመዘገበን የዕፅዋት ዝርያ በአገር ውስጥ አባዝቶ ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሊኖረው ይገባል፡፡

፲፮/ ተቀባዩ አገር የሚጠይቀው የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ ቢኖር ይህንን የሚያረጋግጥ ምስክር ወረቀት  አግባብ ካለው አካል ሊያገኝ ይገባል፡፡

፲፯/ አምራቹ የጥራት ማረጋጋጫ ሰርተፍኬት ከፈለገ በሀገሪቱ አሰራር መሰረት መጠየቅና ማግኘት ይችላል፡፡

፲፰/ አምራቹ የተባዛው ዘር ወደ ውጭ ገበያ መላኩን ለሚኒስቴሩ ማስረጃ ያቀርባል፡፡

## ክፍል አምስት
## የሚኒስቴሩና ተባባሪ አካላት ተግባርና ሃላፊነት

፲፱/ የሚኒስቴሩ ሃላፊነትና ተግባር፡

ሀ/ ይህን ተግባር ሃላፊነት ወስደው ያልተመዘገበ ግን በአገር ውስጥ ተባዝቶ ወደ ውጭ የሚላክን ዝርያ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለማባዛት እና ወደ ውጭ ለመላክ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል፤

ለ/ ወደ አገር ውስጥ የሚገባው የዕፅዋት ዝርያ የአገሪቱ የኳራንታይን ሕግን አሟልቶ መገኘቱን ያረጋግጣል፤

ሐ/ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የዕፅዋት ዝርያዎች በአፈር ላይ ያልተመረቱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

መ/ አምራቹ በሚጠይቀው የዕፅዋት ጤንነት ማረጋገጫ መስፈርት መሰረት ሰርተፊኬት ይሰጣል፤

ሰ/ እንዲባዛ የተፈቀደው ዝርያ ለተፈቀደለት ዓላማና ተግባር መዋሉን ቁጥጥርና ክትትል ያደረጋል፤ ከታለመለት ዓላማ ውጭ ውሎ ሲገኝ በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 በሚደነግገው መሰረት ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ረ/ የተመረተው ዘር ወደ ውጭ መላኩና ተረፈ ምርቱ በተገቢው መንገድ መወገዱን ያረጋግጣል፡፡

፳/ የተባባሪ አካላት የትብብር ማዕቀፍ

የአከባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ፣ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት፣ የኢትዮጵያ ብዝሃ ህይወት፣ንግድና ኢንዱስትሪ፣ ኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤቶች እና በየክልሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሕግ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም በትብብር ይሠራሉ፡፡

፳፩/ መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ20 ቀን 04/2011 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አቶ ዑመር ሁሴን

የግብርና ሚኒስትር